# የረጅም ጊዜ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ምንድን ናቸው፣ እና ለእርስዎ ትክክለኛ ሊሆኑ ይችላሉ?

**Long-term services and supports (LTSS) የተለያዩ  የጤና እና የማህበራዊ አገልግሎቶች**  ናቸው በእድሜ ለገፉ እና እራሳቸውን የመንከባከብ ችሎታቸውን የሚወስን ጉድለት ላለባቸው ሰዎች የአካል፣አእምሮ ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የጤና ሁኔታዎችን ድጋፍ የሚፈልጉትን የሚንከባከብ ነው።LTTS በግለሰብ ቤት ውስጥ፣ በሌላ ማህበረሰብ-መሰረት ያደረገ ስፍራ፣ወይም በተቋም ውሥጥ ሊሰጥ ይችላል። LTSS በእለትተለት አኗኗር እንደ መብላት፣መታጠብ፣ማሥተካከል፣ መልበስ፣መራመድ፣ሽንት ቤት መሄድ፣ ከወንበር ወይም አልጋ ወደላይ/ወደታች ማለት፣እና ምግብ ማዘጋጀትን እርዳታ ይሰጣል።

**LTTS ሊገኝ የሚችለው በ**Columbia ግዛት መንግስት ኤጀንሲዎች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እ ይለያሉ፣ የግለሰብን እንክብካቤ ያቅዳሉ፣እና ስለ LTSS መረጃ ያቀርባል እና ለሱም ምክራዊ አስተያየቶችን ያ ያለባቸው ሰዎች፣በእድሜ የገፉ እና የእነሱ ቤተሰቦች ለተቻለው ጊዜ ያክል በቤታቸው ውስጥ በክብር እንዲኖ በሙሉ እንዲካተቱ የሚያስችላቸውን ስለ LTSS ምርጫ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል።

**ስለ LTSS ሊያዋሯቸው የሚችሉ የግዛቱ የመንግስት ኤጀንሲዎች የሚያካትቱት** the Department of Health Care Finance (https://dhcf.dc.gov/), the Department on Disability Services (https://dds.dc.gov/), the Department of Behavioral Health (https://dbh.dc.gov/), the Department of Human Services (https://dhs.dc.gov/) ፣እና the DC Office on Aging (https://dcoa.dc.gov/)። በተጨማሪ ጥቂት ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ወደ LTSS መዳረሻ ለማቅረብ ከግዛቱ መንግስት ጋር ይሰራሉ።በእነዚህ ድርጅቶች አማካይነት፣ብቁ የሆኑ የግዛቱ ኗሪዎች ለሚከተሉት LTSS መዳረሻ ይኖራቸዋል፣

- የአዋቂ የቀን የጤና መርሀግብሮች
- የእንክብካቤ አስተዳደር
- ለተንከባካቢዎች ድጋፍ
- የህብረት(ቡድን) ምግቦች
- ቤት ድርስ የምግብ አቅርቦት
- መስማት ለተሳናቸው ሰዎች አገልግሎቶች
- የቅጥር አገልግሎቶች
- የቤት ውስጥ ድጋፎች
- ከሆስፒታል መውጣትን ማቀድ
- LTSS ምዝገባ እርዳታ
- ለLTSS ማቀድ የምክር አማራጮች
- የማስታወስ እንክብካቤ ( ለአልዛይመር እና ለአእምሮ መሳት )
- የነርሲንግ ቦታ የዝውውር አገልግሎቶች
- የስነምግብ መርሀግብሮች፣ምክር እና ትምህርት
- የህዝብ ጥቅማጥቅሞች ላይ የማመልከት እርዳታ
- እድሜያቸው ለገፋ የደህንነት ማእከል አገልግሎቶች
- ማጓጓዣ
- የቀድሞ ወታደሮች የድጋፍ ግብአቶች

**የተወሰኑ LTSS አንድ ግለሰብ አገልግሎቶቹን ለማግኘት ሊያሟላቸው የሚገባ የብቃት መስፈርት አለው፣**ይህም ሁለቱንም ገንዘብ ነክ እና ገንዘብ ነክ ያልሆነ መስፈርት ሊሆን ይችላል።ገንዘብ ነክ መስፈርቶች በግለሰብ ገቢ እና ሀብት ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ገንዘብ ነክ ያልሆነው የብቃት መስፈርት የሚያካትቱት የህዝብ ነክ መረጃ እንደ እድሜ እና ጉድለት፣ዜግነት እና የመኖሪያ ሁኔታ፣እና የእንክብካቤ ደረጃ ብቃት። የእንክብካቤ ደረጃ ብቃት የሚወሰነው ፣ግዛቱን በመወከል በሚሰራ የተመዘገበ ነርስ የሚሞላ እና የግለሰቡን የLTTS ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ልዩ  የእንክብካቤ ነጥብ ደረጃን የሚያሰላ አጠቃላይ የጤና ምዘና ነው። ሁሉም LTTS የእንክብካቤ ደረጃ ምዘናዎችን ባይጠይቁም፣ በእንክብካቤ ደረጃ መስፈርት አገልግሎቶች የሚፈልጉ ግለሰቦች በዚህ አጠቃላይ የምዘና ሂደት መሳተፍ አለባቸው።

**LTTS ለእርስዎ ወይም ለሚወዷቸው ትክክለኛ አይነት ድጋፍ መሆኑን ካሰቡ፣ የAging and Disability Resource Center(ADRC) በ DC Office on Aging በማግኘት ይጀምሩ፣**

- በስልክ፣ 202-724-5626
- በኢሜይል፣ Ask.ADRC@dc.gov
- በድህረገጽ፣ www.dcoa.dc.gov

# ከአጠቃላይ የምዘና ሂደት
# እርሶ ምን እንደሚጠብቁ

**InteRAI ምዘና ምንድን ነው?** he InteRAI የግለሰብን የጤና እንክብካቤ እና የድጋፍ ፍላጎቶች መረጃ ለመመዘን መደበኛ ቅጽ ወይም ቃለመጠይቅ ነው። ይህን ምዘና ለማጠናቀቅ ለእርስዎ ጤና ፍላጎቶች፣ግቦች፣እና ምርጫዎችን ለመማር ፍቃድ ባለው ሀኪም የአካል ጉብኝት ማድረግን ያካትታል። ይህ ሂደት ለእርስዎ ምንም ወጪ አያስከትልም፣እና እርስዎ ብቁ ሊሆኑባቸው የሚችሉ የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን (LTSS) ለመለየት ይረዳል። ባብዛኛው ጊዜ LTSS ወይም ምዘና በጠየቁ በ5 ቀናት ውስጥ ይከናወናል።

**ማን ምዘና ማድረግ አለበት?** ጉድለት ያለባቸው በማንኛውም እድሜ ክልል ያሉ ሰዎች ወይም ስር የሰደደ የእንክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸው ሰዎች ምዘና መጠየቅ ይችላሉ።በምዘና ወቅት፣በMedicaid መመዝገብ አያስፈልግዎትም፣ነገር ግን፣በግዛቱ የሚሰጡት አብዛኛው LTTS የሚገኙት በMedicaid አማካኝነት ነው፣እና እነዚህን ፍላጎቶች ለማግኘት ለMedicaid ብቁ መሆን እና መመዝገብ አስፈላጊ ነው።

**ምዘናው እኔን እንዴት ይረዳኛል?** የምዘናው ሂደት ፍላጎቶችዎን በተቻለ ሁኔታ እንዲረዱ እና እነዚያን ፍላጎተተ ለማሟላተ አገልግሎተተ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ያስችሎታል።እንደነዚህ አይነት ፍላጎቶች ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ወይም ከሆስፒታል ወይም የነርሲንግ ቤት ወደቤትዎ እንዲዛወሩ ሊረዳዎ ይችላል። በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግበት LTSS ብቁ ከሆኑ፣እነዚያን አገልግሎቶች እንዲለዩ እና እንዲመዘገቡ ይረዳዎታል።ለተወሰኑ መርሀግብሮች ብቁ ካልሆኑ፣አማራጭ አገልግሎቶችን እንዲለዩ ይረዳል።

**የኔ ምዘና ላይ ማን ሊገኝ ይችላል? መዛኙ ምን ይጠይቀኛል?** የእርሶ የቤተሰብ አባሎች፣ ህጋዊ ወኪል ወይም ሌላ በህይወትዎ አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች ምዘናው ላይ መገኘት እና መረጃ እንዲሰጡ እርስዎን መርዳት ይችላሉ። መዛኙ ሊጠይቀኝ የሚችላቸው ጥያቄዎች የሚያካትቱት፣

- የእለትተለት ፍላጎቶችዎን እንደ መልበስ፣ መመገብ፣ ገላ መታጠብ እና ወዲያ ወዲህ ማለቱን እንዴት እንደሚያስተዳድሩ
- በመደበኛ ሁኔታ የሚያገኝዋቸው ወይም በቅርቡ የተጠቀሙት የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች
- እንደመረጡ የመኖር ችሎታዎ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ የጤና ስጋቶች ወይም ፈተናዎች
- የት እና እንዴት መኖር እንደሚፈልጉ፣እንደሚሰሩ እና በማህበረሰብ ውስጥ እንደሚሳተፉ

በተጨማሪም ለምዘናው የመድሀኒቶችን ዝርዝር ወይም የመድሀኒት ጠርሙሶችን፣ የጤና አገልግሎቶች ሪከርዶች፣ወይም ለተሟላ የጤና ታሪክ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል ሌላ መረጃ በመሰብሰብ ሊዘጋጁ ይችላሉ።

**ከምዘናው በኋላ ምን ይፈጠራል? ውጤቶችንስ መቼ አውቃለሁ?** ከምዘናው በኋላ፣ በጉብኝትዎ ወቅት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የተመደበሎትን ልዩ  ውጤት ይነገርዎታል። የጽሁፍ መረጃ ይደርስዎታል የሚያካትተውም፣

- አጠቃላይ የምዘና ነጥብዎ እና የነጥቦች ክፍል መለኪያ
- ይህን ተግባራዊ ምዘና የሚጠይቀው የLTSS የብቃት መለኪያ፣በምዘናው መሰረት ለየትኛው ብቁ እንደሆኑ ሊለዩ  እንዲችሉ
- ስለ LTSS ያሉ መረጃ እና ፍላጎቶችዎን እንዲያሟሉ እንዴት እንደሚረዱ

ለግዛቱ የMedicaid ነጻ መርሀግብር ብቁ ከሆኑ እና ለመመዝገብ ከመረጡ፣ እርስዎን በመወከል ሪፈራል ያደርጋል እና በLTSS እቅድ እና ምዝገባ ለመረዳት የጉዳይ አስተዳደር ኤጄንሲ እርሶን ያገኛሉ።

**ምን መብቶች አሉኝ?** ለምዘናዎ አስተርጓሚ የመጠየቅ እና የጤና መረጃዎን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ መብት አሎት። በተጨማሪ የምዘና ውጤቶች ላይ ካልተስማሙ ይግባኝ ሊሉ ይችላሉ።

**ለLTSS ምዘና መጠየቅ ከፈለጉ፣የAging and Disability Resource Center(ADRC) በ DC Office on Aging በማግኘት ይጀምሩ፣**

- በስልክ፣ 202-724-5626
- በኢሜይል፣ Ask.ADRC@dc.gov
- በድህረገጽ፣ www.dcoa.dc.gov

# ከምዝና በኋላ፤ ቀጥሎ ምንድን ነው?

ምዘና ካደረጉ በኋላ እና ውጤትዎን ከተቀበሉ፣ የረጅም ጊዜ አገልግሎት እና ድጋፍ(LTSS) የአማራጭ እድሎችዎን መመዘን እና የእርሶን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን፣ግቦች እና አማራጮች ለማሟላት ትክክለኛ ድጋፎች የትኞቹ እንደሆኑ መወሰን ይችላሉ።ለጥቂት LTSS ለአገልግሎቶቹ የተግባር ብቃትን እንዲያሟሉ ፣ የምዘና ነጥብዎ በቁጥር ከሚለካ መለኪያ እኩል ወይም  የበለጠ ሊሆን ይገባል። በተጨማሪ፣ በMedicaid ባሁኑ ጊዜ የተመዘገቡ ካልሆኑ፣ለLTSS ልዩ  የሆነውን ሌላ የብቃት መስፈርቶች ማሟላት ለማረጋገጥ ከጉዳይ አስተዳዳሪ ጋር ወይም ከግዛቱ የመንግስት ባልደረባ ጋር መስራት ሊያስፈልግዎ ይችላል።

**ምዘናውን ከሞሉት ነርስ ያገኙት ደብዳቤ ላይ ያለውን የምዘና ነጥብ ይመልከቱ።**

**የተለጠፈው አጠቃላይ የምዘና ነጥብዎ <u>9 ወይም ከፍተኛ ከሆነ</u>**፣ ለሚከተሉት አገልግሎቶች የተግባር መስፈርቶች ያሟላሉ፣

- *የነርሲንግ ተቋም አገልግሎቶች።* የነርሲንግ ተቋሞች የሰለጡኑ የነርሲንግ ወይም የህክምና እንክብካቤ፣ከጉዳት፣ ጉድለት ወይም በሽታ በኋላ የሚፈለገውን የመልሶ ማቋቋም እንክብካቤ እና የአእምሮ ወይም የአካል ሁኔታን ለረጅም ጊዜ በመደበኛ ሁኔታ ለመንከባከብ የሚያስፈልገውን ያቀርባሉ።
- *Elederly and Persons with Physical Disabilities Waiver (EPDWaiver) አገልግሎቶች፡*የEPD ነጻ መብት ብቃትላላቸውበእድሜ የገፉ አዋቂዎች እና በቤታቸው ውስጥ ወይም በማህበረሰብ የሚኖሩ ጉድለት ላለባቸው ግለሰቦች የተደራጀ የLTSS ያቀርባል፣ ይህም የሚያካትተው የጉዳይ አስተዳደር፣ የግል እንክብካቤ ረዳት አገልግሎት፣ የአዋቂ የቀን የጤና መርሀግብሮች፣ የግል የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሲስተም(PERS)፣የእረፍት እንክብካቤ፣ድጋፍ ያለው አኗኗር እና ለአካባቢ ተደራሽ የሆነ መላመዶች
- *Personal Care aide(PCA) አገልግሎቶች ከEPD ነጻ መብት ውጪ።* PCA አገልግሎቶች በEPD ነጻ መብት ላልተመዘገቡ ግለሰቦች ይገኛል። እንደዚህ አይነት አገልግሎቶች ምልክት መስጠትን እና የእለትተለት የአኗኗር እንቅስቃሴዎች እንደ ገላ መታጠብ፣መንቀሳቀስ፣ መመገብ፣ወይም መታጠቢያ ቤትን መጠቀም ላይ እርዳታ መስጠትን ያካትታል።
- *Adult Day Health Program(ADHP) አገልግሎቶች ከEPD ነጻ መብት ውጪ።* የADHP አገልግሎቶች በእድሜ ለገፉ አዋቂዎች በመኖርያ አካባቢ ያልሆነ የህክምና ድጋፎችን እና ማህበረሰብ-መሰረት ያደረገ ወይም በቡድን ስፍራ ቁጥጥር የሚደረግበት የቴራፒ እንቅስቃሴዎችን ያቀርባል። ግለሰቦች የተግባር የብቃት መለኪያዎችን ካሟሉ ቢመዘገቡም ወይም ባይመዘገቡም የADHP አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ።.

**አጠቃላይ የምዘና ነጥብዎ <u>በ 4 እና 8 መካከል ከሆነ</u> ወይም ከፍተኛ ከሆነ**፣ለሚከተሉት አገልግሎቶች የተግባር መስፈርቶች ያሟላሉ፣

- *Personal Care aide(PCA) አገልግሎቶች ከEPD ነጻ መብት ውጪ።* PCA አገልግሎቶች በMedicaid ለመመዝገብ መስፈርቶችን ካሟሉ እና ከመድህኒት አስተዳደር ውጪ የተግባር ምዘና ውጤትዎ 4 ወይም ከፍተኛ ከሆነ ለEPD ነጻ መብት ብቁ ላልሆኑ ግለሰቦችም ይሆናል፣ የመድህኒት አስተዳደር በPCA አገልግሎቶች ውስጥ የተካተተ አገልግሎት አይደለም።PCA አገልግሎቶች ምልክት መስጠትን እና እንቅስቃሴዎችን እንደገላ መታጠብ፣ መንቀሳቀስ፣መመገብ፣ወይም መታጠቢያ ቤት መጠቀም ላይ እርዳታ ይሰጣል።.
- *Adult Day Health Program(ADHP)አገልግሎቶች ከEPD ነጻ መብት ውጪ።* የADHP አገልግሎቶች በMedicaid ለመመዝገብ መስፈርቶችን ካሟሉ እና የተግባር ምዘና ውጤትዎ 4 ወይም ከፍተኛ ከሆነ ለEPD ነጻ መብት ብቁ ላልሆኑ ግለሰቦችም ይሆናል።ውጪ።የADHP አገልግሎቶች በመኖርያ አካባቢ ያልሆነ የህክምና ድጋፎችን እና ማህበረሰብ-መሰረት ያደረገ ወይም በቡድን ስፍራ ቁጥጥር የሚደረግበት የቴራፒ እንቅስቃሴዎችን ያቀርባል።

**አጠቃላይ የምዘና ነጥብዎ <u>በ0 እና 3 መካከል ከሆነ</u>፣** ወይም ከመድህኒት አስተዳደር ውጪ የተግባር ምዘና ውጤትዎ በ 0 እና 3 መካከል ከሆነ፣ካላይ ላሉት አገልግሎቶች በMedicaid መርሀግብር ብቁ አይደሉም። ነገር ግን፣ ለሌሎች LTSS፣ እንደ የሰለጠነ የነርስ እንክብካቤ በቤት ውስጥ፣ የተንከባካቢ ድጋፎች፣ በህብረት እና ቤት ድረስ የሚቀርብ ምግቦች፣መስማት ለተሳናቸው አገልግሎቶች፣የቅጥር አገልግሎቶች፣ የስነምግብ እና የደህንነት መርሀግብሮች፣ የማጓጓዣ ጥቅማጥቅሞች፣ወይም የቀድሞ ወታደሮች የድጋፍ ግብአቶችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። **አማራጭዎችዎን ለመመዘን ለተጨማሪ እርዳታ፣የAging and Disability Resource Center(ADRC) በ DC Office on Aging በማግኘት ይጀምሩ፣በስልክ፣202-724-5626 ወይም በኢሜይል፣Ask.ADRC@dc.gov ያግኙ።.**